## ሽመልስ አብዲሳ ማነው?

በዚህ አጭር ጽሁፍ የሽመልስ አብዲሳን የጉልምስና የሕይወት ጉዞ በጥቂቱ እንዳስሳለን። በአዲስ አበባ ጥቂት ኢትዮጵያውያንን ተጠግቶ ከጀመረው የማደጎ ኑሮ እንነሳለን። ከዚያ በፊት አምቦ ተማሪ እንደነበር ይታወቃል። ትርክቱ ኑሯቸውን በአሜሪካ አድርገውና በመጨረሻም ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ባቀዱ ሁለት ጓደኛሞች በጎ ስራ ይጀምራል። ይህ በጎ ስራ የሽመልስን ሕይወት የቀየረ ነበር። ጓደኛሞቹ አቶ ሃይማኖት ላቀው እና ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ ናቸው። ቦስተን ከተማ ይኖር የነበረው አቶ ሃይማኖት ላቀው አዲስ አበባ ውስጥ ቤት ይሰራና እቃዎቹን ያጓጉዛል። ጓደኛው ዶክተር ዳኛቸው ከእርሱ ቀደም ብሎ አገሩ ይገባል። ጊዜው በኢሕአዴግ የአገዛዝ ወቅት ነበር። አቶ ሃይማኖት ዝግጅቱን ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ሀገሩ በመጓዝ መኖሪያ ቤቱ ይገባል። ቤቱን እና ንብረቱን የሚጠብቅለት ሰው ማፈላለግ እንደጀመረ ለጓደኛው ለዶክተር ዳኛቸው ያወያየዋል። ዶክተር ዳኛቸው ሲያሰላስል ቆይቶ አንድ ሀሳብ ያቀርብለታል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምረውን አንድ ችግረኛ ተማሪ እየረዳኸውና እያስተማርከው ለምን ቤትህን እንዲጠብቅልህ አታደርግም ይላል። አቶ ሃይማኖት በሃሳቡ ከተስማማ በኋላ ዶክተር ዳኛቸው ለተማሪው ይነግረዋል። ተማሪው በደስታ ፈቃደኛነቱን ይገልጻል። ያ ችግረኛና እርዳታ ይሻ የነበረው ተማሪ አቶ **ሽመልስ አብዲሳ፣** የአሁኑ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ ብሔር ነው።

የዶክተር ዳኛቸውን ምክርን ተቀብሎ ሽመልስ በደስታ በአቶ ሃይማኖት ቤት መኖር ይጀምራል። ከትምህርቱ ውጭ ባሉት ጊዜያት እየተላላከና የቤት ስራ እየሰራ ኑሮውን ከዩኒቨርሲቲ ትምህርቱ ጋር ያካሂዳል። ሽመልስ እቤት በማይኖርበት ሰዓት ቤቱ መጠበቅ ስላለበት የአቶ ሃይማኖት ወላጆች አንድ ዘመዳቸውን ከመንዝ ያመጡና እርሱም እዚያ ቤት ኗሪ ይሆናል። ሽመልስ ከዚህ ሰው ጋር ክፍል ተጋብሎ መኖር ይጀምራል። ዶክተር ዳኛቸው ወደዚህ ቤት ሲመጣ ሽመልስ ለሁለቱ ጓደኛሞች በሚያሳየው ጠባይ፣ የስራ ትጋትና ቅልጥፍና እንዲሁም መላላክ ስሙ ተደጋግሞ መጠራት ይጀምራል። ደባሉ መንዜው ከባላገር የመጣና ከተማ ቀመስ ስላልሆነ ሲጋራ፣ ቢራ፣ ኮካ ኮላ፣ ወዘተርፈ፣ ከሱቅ ለመግዛት የሚላከው ሽመልስ ብቻ ይሆናል። በዚህም የተነሳ በሽመልስ ላይ ጥላቻ ያድርበታል፣ የማይገቡ ቃላትን፣ ጎሳ ተኮር ስሞችን ጨምሮ፣ መጠቀም ይጀምራል። ይህ ምንአልባት ከአምቦ ለመጣው የሽመልስ ሕሊና ላይ ያሳደረው ትልቅ ተጽዕኖ ሊኖር ይችላል ብለን ልንገምት እንችላለን።

በአሜሪካ ይኖር የነበረው አቶ ብርሃኑ ዳምጤ ወደ ኢትዮጵያ ከሄደ በኋላ አቶ ሃይማኖትን ሊጠይቅ ይሄዳል። እዚያ ቤት የሚኖረውን ሽመልስ አብዲሳን ይተዋወቃል። ሽመልስ ለእርሱም ሲጋራና ሌሎች ቁሳቁሶችን ከሱቅ በመግዛት ይላላክለት ጀመር። በቤቱ ውስጥ ለዚህ ዓይነቱ ስራ ሁሌ የሚፈለገው ሽመልስ በመሆኑ የመንዜው ብስጭት እየጨመረ ይሄዳል፣ ዘመናዊ ትምህርት አለመማሩ በቋንቋ በኩል እንደጎዳውም ይረዳል ሆኖም ሽመልስ ላይ የነበረው ጥላቻ አላባራም። ለጥቂት ቀናት ያህል የሽመልስን ሁኔታ የተገነዘበው አቶ ብርሃኑ ባህርዩን እና ፈጣንነቱን በማየት ስራ ሊያስቀጥረው ያስባል። አቶ ብርሃኑ ወይዘሮ አቡዬ የሚባሉ የአማቱ ጎረቤት ከሆነችው ሰው ቤት ከምትመጣው የአባዱላ ገመዳ ሚስት ጋር ይተዋወቃል። የአቶ ብርሃኑ ባለቤት የወይዘሮ ኤልሣቤጥ በቀለ አባት በሞቱበት ወቅት ጎረቤት ማዕድ ሲቋደስ እነአባ ዱላም እንዲሁ ሀዘንተኛውን ራት በመጋበዝ (በባህሉ ቁርስ፣ ምሣ፣ ራት፣ ማብላት ይሉታል) ይተዋወቃሉ። የብርሃኑ ዳምጤ እናት በጎሳ ኦሮሞ በመሆናቸው ቤተሰቡ ከአባ ዱላ ቤተሰብ ጋር ፈጣን የሆነ ግንኙነት ይፈጥራል። ብርሃኑም ጊዜ ሳይፈጅ አንድ ችግረኛ የአምቦ ልጅን ስራ እንዲያስይዘው አባዱላን ይጠይቃል። ልጁ በጣም ቀልጣፋና ተግባቢ መሆኑንም ጨምሮ ይገልጻል። የአባዱላን እሺታ ሲያገኝ ብርሃኑ ወዲያውኑ ለሽመልስ ስልክ ደውሎ አባዱላን እንዲያነጋግር ያደርጋል፣ ንግግሩ በኦሮምኛ ነበር። ሽመልስ አባዱላን በደምብ እንደሚያውቃቸው እና ስራቸውን ሁሉ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ አወዳድሶ ይናገራል። አባዱላ በማግስቱ ጠዋት ቦሌ መንገድ የሚገኘው ቢሮዬ ናና እንነጋገራለን ብሎ ሲቀጥረው የስልክ ንግግሩን ያዳምጥ የነበረው ብርሃኑ ግዴለም እኔ ይዤው እመጣለሁ በማለት በነገታው ይዞት ይሄዳል።

አባዱላ ከእኔ ጋር ትሰራለህ ብሎ ሽመልስን ቀጠረው፣ ቢሮም ሰጠው። ሽመልስ በአቶ ሃይማኖት ቤት እየኖረ ሳለ የወይዘሮ ኤልሳቤጥ እናት ሾፌር ሽመልስን መኪና መንዳት አስተምሮት ስለነበር ከጊዜ በኋላ ፓጃሮ መኪና እየነዳ መምጣት ጀመረ። ከደባሉ እና ከመንዜው ጋር አለመግባባቱ እያየለ ሄዶ ሽመልስ አንድ ችግር ያመጣብኛል ብሎ በማሰብ መንዜው አዲስ አበባን ለቆ አገሩ ገባ። ይህን የሁለቱን ሰዎች ግጭት የተገነዘበችው የአቶ ሃይማኖት ባለቤት ***"ልጄን እንዲህ አድርገህ ታጠግብበን ወይ"*** ብላ ቅሬታ ማቅረብ ጀመረች። ሽመልስ የኦሮሚያ ታርጋ ያላቸውን መኪናዎች ማፈራረቅ ጀመረ። የአባ

ዱላ ቀኝ እጅ እየሆነም ሄደ። ከዶክተር አቢይ ጋር የተዋወቁትም እዚያው አባ ዱላ ቤት ነበር። በዚያን ጊዜ ታዛዥነቱን ዶክተር አቢይ የተገነዘበ ይመስላል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ ከመሾሙ በፊት የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድን ርዕሰ መስተዳድር ጨምሮ በተለያዩ የስራ ኃላፊነቶች አገልግሏል። ለምሳሌ በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ ሲያገለግል የነበረውን አቶ ፍፁም አረጋን በመተካት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆኖ አገልግሏል። ሚያዚያ 10 ቀን 2011 ዓም የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት አቶ ሽመልስን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አድርጎ የሾመው አቶ ለማ መገርሳን አስወግዶ ነበር። ሽመልስን ለመተካት ምርጫው እንዲደረግ ጥሪ አቅርቦ የነበረው የኦሮሚያ ራዲዮ ሥርጭት መስተዳድር ነበር። ለማ መገርሳ "***ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው***" ብሎ በተናገረበት መድረክ ላይ ሽመልስ ከኋላው ቁጭ ብሎ የጎሪጥ ያየው ነበር። የእርሱን ወምበር የከጀለበት ያ ጊዜ ይሆን?

የአባዱላ ባለቤት ወይዘሮ ራሄል ሽመልስን "***በጣም ጥጋበኛ ሰው ነው፣ ትከሻውን ያሳየኛል***" እያለች ለወይዘሮ አቡዬ ጎረቤት ይህንኑ እየተናገረች ዜናው አሜሪካ ለሚኖረው ለአቶ ብርሃኑ ዳምጤ መድረስ ጀመረ። አቶ ብርሃኑ ዳምጤ በድጋሚ ወደኢትዮጵያ ሲሄድ ሽመልስጋ ስልክ ደውሎ "*እንገናኝለን*" ብሎት ሳያገኘው ዋለ አደረ። ስልኩንም ዘጋ፣ ከነጭራሹም ቀየረው። የቀድሞ አሳዳሪውን አቶ ሃይማኖት ላቀውንም እንዲሁ ራቀው። ለምን ይፈልጋቸዋል? አንዴ ቆጥ ላይ ሰቅለውታል! የሽመልስ የአማራ ጥላቻ እዚያ ቤት ጀምሮ ይሆን? "***የሰበሩንን ሰበርናቸው ወይም የሰበሩኝን ሰበርኳቸው***" ሲል ከዚህ ጋር ይገናኝ ይሆን? እነዚህ ድርጊቶቹስ ምን ያሳዩናል? በእርሱ የአስተዳደር ዘመን በኦሮሚያ የተጨፈጨፉትን የአማራ ዝርያዎች መቁጠር አይቻልም። እንደ ሕዝብ አስተዳዳሪ ምንም ዓይነት እርምጃ አለመውሰዱ የጭካኔውን ጥግ ሲያሳይ ውድቀቱንም ጠቋሚ ነው።

በደርግ የአገዛዝ ዘመን በተመሳሳይ መንገድ ስልጣን ላይ ወጥቶ እና የአንድ ክፍለ ሀገር የደህንነት ቢሮ ዋና ኃላፊ የነበረን ሰው ያስታውሰናል። ያ ሰው ለዚያ ስልጣን የበቃው ለደርግ አገዛዝ ፍጹም ታዛዥ በመሆን ብዙ የፖለቲካ እስረኞችን በማስገደል ነበር። እንደ ሽመልስ ተሰፈኛ ነበር። ያ ሰው ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ተይዞ የገደላቸውና ያስገደላቸው ሰዎች የተቀበሩበትን ቦታ ጅማ እና አካባቢ ውስጥ እየመራ ያሳይ ነበር። የሽመልስ እጣ ከዚህ የሚለይ አይሆንም፣ ልዩነቱ መጥፊያው ብቻውን አለመሆኑና ከግብረ አበሮቹ ጋር መሆኑ ነው።